## ቶማስ S. ውተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት / በቤተሰብ የቀረቡ ጥያቄዎች እና መልሶች

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| ትምህርት ቤቱ በሚቀጥለው ቀን (ፌብሩዋሪ 10) ሥራውን የጀመረበት ምክንያት ምንድን ነው? | ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ተማሪዎችና ሰራተኞች በተዋቀረ እና ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ የምክር/የካውንስሊንግ አገልግሎት፣ የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ጋር መገናኘት፣ ከሚታመኑ አዋቂ ሰዎች እና ከእኩዮቻቸው ድጋፍ እንዲያገኙ ስለሚያስችላቸው ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ግንኙነት ማድረግና ድጋፍ ማግኘት የስሜት ቀውስን በመቀነስ ማህበረሰቦችን ከተፈጠረባቸው ስጋት እንዲድኑ ይረዳል።<br>በእለቱ ትኩረት የተደረገው በአካዳሚክ ትምህርት ላይ ሳይሆን ስሜታቸውን የማረጋጋት ድጋፍ በመስጠት ላይ ነበር። |
| የጦር መሳሪያው ወደ ህንፃው እንዴት ሊገባ ቻለ? | ከተኩሱ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች እስካሁንም የፖሊስ ምርመራ እየተካሄደባቸው ነው። MCPS እና የህግ አስከባሪዎች የደህንነት ጥበቃ ስርዓቶችን እና ሂደቶችን ጨምሮ ሁሉንም መረጃዎችን እየገመገሙ ናቸው። ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ ወቅታዊ መረጃዎች ይጋራሉ። |
| በውተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወዲያውኑ የተወሰዱት የደህንነት እርምጃዎች ናቸው? | MCPS በውተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስዷል፦<br>● MCPS በቦታው ላይ የደህንነት ጥበቃ ሰራተኞችን ቁጥር ከስድስት ወደ 10 ሰራተኞች ቁጥር ጨምሯል።<br>● በትምህርት ቤቱ ውስጥ በየቀኑ የፖሊስ አባላት እንዲገኙ ተደርጓል።<br>● ተጨማሪ ካሜራዎች እንዲገጠሙ እና የተሰወሩ ቦታዎችን የእይታ ክፍተቶች በግልፅ በካሜራዎች እንዲታዩ ተደርጓል።<br>● የኤሌክትሮኒክስ በር መቆለፊያ ስርዓቶች እንዲሻሻሉ ተደርጓል።<br>● ወደ ት/ቤት ህንፃዎች የመግቢያ ሂደቶች ላይ የማጠናከሪያ እርምጃ ተወስዷል።<br>● ከሁሉም ተማሪዎች ጋር ቀልፎ የመከላከል የአደጋ ጊዜ መከላከል ፕሮቶኮሎችን ገምግሟል።<br>● ተማሪዎች በአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን ማግኘታቸውን አረጋግጠናል።<br>● የአእምሮ ጤና ድጋፎች በስፋት እንዲሰጡ |

| | |
|---|---|
| | ተደርጓል። <br><br> የደህንነት አጠባበቅ ሥርአት ማሻሻያዎች ይቀጥላሉ። |
| MCPS ብረት ነክ ነገሮችን ወይም የጦር መሳሪያ መመርመሪያ ስርዓቶችን ይጠቀማል? | MCPS የጦር መሳሪያ መፈተሻ ቴክኖሎጂዎችን በንቃት እየተመለከተ ሲሆን [በዚህ የጸደይ/ሠመር ወቅት በሦስት MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ]() ሙከራዎች ይደረጋሉ። እነዚህ መሳሪያዎች የሰው ኃይል፣ የመሠረተ ልማት፣ ውጤታማነት፣ እና በማህበረሰብ ላይ የሚያሳድሩ ተጽዕኖዎችን ስለሚያካትቱ ጥንቃቄ የተሞላበት ግምገማ ያስፈልጋቸዋል። <br> ነገር ግን አደጋዎችን በሙሉ የሚያስወግድ አይነት ብቸኛ መፍትሔ የለም። MCPS በአካል የደህንነት ጥበቃን፣ የሰለጠኑ ሰራተኞችን፣ የአደጋ ጊዜ መከላከያ ሂደቶችን፣ ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር በጋራ መሥራት እና ጠንካራ የትምህርት ቤት ግንኙነቶችን የሚያካትት ሁሉን አቀፍ የደህንነት ጥበቃ ተግባሮችን ይጠቀማል። |
| በውተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመግባት መደበኛ የደህንነት ጥበቃ ሂደቶች ምንድናቸው? | መደበኛ የመግቢያ ሂደቶች የተዘጉ የመግቢያ በሮች፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የህንፃዎች መግቢያዎች፣ በስውር ክትትል የማድረግ ስርዓቶች፣ በሰራተኞች የሚደረግ ቁጥጥር እና የውጭ በሮች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ የሚዘጉ መሆናቸውን ያካትታሉ። በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ሂደቶች እየተገመገሙና እየተጠናከሩ ናቸው። |
| ይህ በውተን ብቻ የተከሰተ ጉዳይ ነው ወይስ ስርዓት አቀፍ የደህንነት ስጋት ነው? | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ የትምህርት ቤት ደህንነት በስርዓት አቀፍ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በቅርብ ጊዜ በዲስትሪክቱ ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተካሄዱ የደህንነት ጥበቃ ኦዲቶችን ለመመለስ፣ MCPS ከህንፃ ደህንነት፣ ከአደጋ ጊዜ የመከላከል ሂደቶች እና ከአሠራር ልምዶች ጋር የተያያዙ ማሻሻያዎችን በንቃት ተግባራዊ እያደረገ ነው። <br><br> እንዲሁም በሁሉም ትምህርት ቤቶች መደበኛ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮሎችን (SRP) አጠናክረናል። ይህም የአምስቱ ዋና ዋና የአደጋ ጊዜ ምላሾችን መደበኛ ስልጠና እና ልምምድ ያካትታል፡ <br><br> ● ቆልፎ መከላከል — በህንፃው ውስጥ ወይም በአቅራቢያ ካለ ስጋት በፍጥነት መከላከል። <br> ● በሮችን ቆልፎ — በውስጡ መደበኛ ስራዎችን |

| | |
|---|---|
| | መቀጠል<br>● ባሉበት መቆየት — ሁኔታዎች እስኪረጋጉ ድረስ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ወይም ባሉባቸው ቦታዎች እንዲቆዩ ማድረግ።<br>● ከአካባቢው መልቀቅ — ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ደህንነቱ ወደ ጠበቀ ቦታ ማዛወር።<br>● ከለላ መያዝ — ከአካባቢያዊ ወይም ከውጭ አስጊ አደጋዎች ለመከላከል ከለላ መያዝ።<br><br>እነዚህ ፕሮቶኮሎች ከተማሪዎችና ከሠራተኞች ጋር በመደበኛነት የሚተገበሩ ሲሆን በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች ግልጽና ወጥ የሆነ ምላሽ ለመስጠት የተነደፉ ናቸው።<br><br>MCPS የደህንነት አጠባበቅ ሂደቶችን ያለማቋረጥ ይገመግማል፣ የኦዲት ግኝቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ የመማሪያ አካባቢዎችን ለማረጋገጥ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የደህንነት እርምጃዎችን ያጠናክራል።<br><br>ቤተሰቦች ስለ MCPS የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮሎች እዚህ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።<br>እንዲሁም -- ይመልከቱ:-<br>የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዝግጁነት<br>ስለ MCPS መደበኛ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮቶኮል የሚያግዝ መረጃ |
| አዳዲስ የትምህርት ቤት መገልገያዎች ወይም ሕንፃዎች የተሻሻሉ የደህንነት አጠባበቅ ሥርዓት ያካትታሉ? | ደህንነት እና የደህንነት አጠባበቅ ሲስተም መዘርጋት በአዲሱ የትምህርት ቤት ግንባታ እና ነባር የትምህርት ቤት ስራዎች ውስጥ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተነደፉት እና የሚተዳደሩት በርካታ የደህንነት ጥበቃና መከላከያ ደረጃዎችን በመጠቀም ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ፡<br><br>● በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚገኙ መግቢያዎች እና መተላለፊያ ቦታዎች ለደህንነት ጥበቃ እና ለመቆጣጠር አመቺ ይሆናሉ።<br>● የጎብኚዎች አስተዳደር ስርዓት፣ ጎብኚዎችን የመፈተሽ እና መግቢያ በሮች ላይ የወንጀል ዳራ ፍተሻዎች የሚደረጉበት ሥርዓት ነው። |

| | |
|---|---|
| | • MCPS መደበኛ የምላሽ አሰጣጥ ፕሮቶኮሎች (LOCKDOWN፣ SECURE፣ HOLD፣ EVACUATE፣ SHELTER) ተግባራዊ ማድረግ፣ እነዚህም በተማሪዎችና በሠራተኞች በመደበኛነት ይከናወናሉ።<br>• የደህንነት እና የአደጋ ጊዜ መከላከል ሂደቶችን ለማስፈፀም ዝግጁ የሆኑ የሰለጠኑ የትምህርት ቤት ሰራተኞች።<br>• በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጠንካራ የሆኑ የደህንነት ጥበቃ ቡድኖች፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመካከለኛ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ የጸጥታ ሰራተኞችን መጨመር። |
| ወደፊት ስንት የፖሊስና የደህንነት ሰራተኞች ይኖራሉ? | ከላይ እንደተጠቀሰው፣ MCPS በውተን ት/ቤት ከስድስት ወደ 10 የደህንነት ጥበቃ ቡድን አባላት ቁጥር ጨምሯል፣ እናም ይህ የተጨመረው የሰው ኃይል ደረጃ በውተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት አመት ለቀሪው የትምህርት ጊዜ በቦታው በሥራ ላይ ይቆያል።<br><br>በተጨማሪም፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የፖሊስ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ስላለ ይቀጥላል። MCPS ከአካባቢው የህግ አስከባሪ አካላት ጋር በቅርበት መስራቱን ይቀጥላል እንዲሁም ተገቢ የሆኑ የደህንነት እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የት/ቤቶችን የደህንነት ፍላጎቶች በየጊዜው ይገመግማል። |
| ወላጆች የትምህርት ቤትን ደህንነት ለማሻሻል ምን ማድረግ ይችላሉ? | ደህንነት የሁላችን የጋራ ኃላፊነት ነው። ቤተሰቦች የሚከተሉትን በማድረግ በመከላከል ረገድ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡-<br>• ተማሪዎች ለሚያምኗቸው አዋቂዎች ስጋታቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉ ማበረታታት። ስጋቶችን ሪፖርት ማድረግ የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳል የሚለውን መልእክት ማጠናከር።<br>• ማህበራዊ ሚዲያን እና የኦንላይን እንቅስቃሴዎችን መከታተል እና መቆጣጠር።<br>• ስለ ትምህርት ቤት ደህንነት ተጠባቂ ነገሮችን ማስረዳት እና ማጠናከር።<br>• "Safe Schools Maryland tip line (1-833-MD-B-SAFE)" ክፍት የጥሪ መስመርን መጠቀም። |

| | |
|---|---|
| ስለዚህ ክስተት MCPS ድረ ገጽ ላይ ያለው መረጃ ውስን የሆነው ለምንድን ነው? | MCPS ተኩስ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እና በቀጣዮቹ ቀናት ውስጥ በተከታታይ በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች አማካኝነት ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች፣ እና ከቤተሰቦች ጋር በቀጥታ መረጃዎችን አጋርቷል። የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ፣ መመሪያ፣ እና የሚገኙ ግብዓቶችን ማግኘቱን ለማረጋገጥ እነዚህ ወቅታዊ መረጃዎች የተላኩት በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት እና በትምህርት ቦርድ ፕሬዝዳንት ነው።<br><br>የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን በማረጋጋት፣ በመደገፍ እና ወደ መደበኛ ስራቸው ለመመለስ እየሠራ ግንኙነቱን በየጊዜው ይቀጥላል።<br><br>በተለይ ከወንጀል ምርመራው ጋር የተያያዘ መረጃ — ስለ ክስተቱ ራሱ ዝርዝሮችን ጭምር — በሮክቪል ከተማ ፖሊስ መምሪያ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ስቴት አቃቤ ህግ ቢሮ ጭምር በሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች አማካኝነት ይተላለፋል። MCPS የተረጋገጡ መረጃዎች እና ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ወቅታዊ መረጃዎች ሲደርሱን እና ለማጋራት ተገቢ ከሆኑ ማጋራቱን ይቀጥላል። |